# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

## ዜና ሕይወቱ ለብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ

የከንባታ፣ ሐድያ፣ ጉራጌ እና ሥልጢ አኀጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ከአባታቸው ከመምሬ ክንፈ መካኤል ወልደሰንበት እና ከእናታቸው ከወ/ሮ አስካለ ማርያም ወልደ መስቀል ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በምሁር ገዳም አካባቢ ተወለዱ።

የአሁኑ አቡነ መልከጼዴቅ የዛን ጊዜው ሕፃን ኃይለኢየሱስ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ምሁር ገዳመ ኢየሱስ ገብተው ከፊደለ ሐዋርያ እስከ ግብረ ዲቁና ያሉትን ትምህርቶች ከተማሩ በኋላ በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. በጊዜው የቤተክርስቲያናችን ፓትሪያርክ ከነበሩት ከብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዲቁና ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ በገዳመ ምሁር እና በአካባቢው በዲቁና እየተዘዋወሩ ካገለገሉ በኋላ በ1972 ዓ.ም. የዝዋይ ገዳም የመጀመሪያውን ዙር የሥልጠና ዕድል አግኝተው ወደ ዝዋይ አቀኑ። ዝዋይ ገዳም ከወረዱ በኋላ በጊዜው ከነበሩት ከብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ጋር ቁጭ ብለው በመማር በስብከተ ወንጌል መረብ ብዙ ምዕመናንን የሚያጠምዱ የወንጌል ገበሬ ለመሆን በቁ። ብጹዕነታቸው መደበኛውን የዝዋይን ሥልጠና እንደፈፀሙ ከመመለስ ይልቅ በዚያው ጸንተው በገዳሙ ካሉ መምህራን ሀዋትያ ዜማ መዝገብ ቅዳሴ እና ቅኔ ተምረዋል። ከዚህም ጋር ጎን ለጎን በስብከተ ወንጌል እንደ ሐዋርያት በመሰማራት ሥጋና ነፍስን በሚያረካ ትምህርታቸው ወጣቶችን ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን መልሰዋል። በዚህ አገልግሎትና የትምህርት ጊዜ በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ለ8 ዓመታት ያህል ከቆዩ በኋላ በ1978 ዓ.ም. ወደ ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው ለ4 ዓመታት ያህል የነገረ መለኮት ትምህርታቸውን አጠናቅቀው በ1981 ዓ.ም ከኮሌጁ እንደወጡ በመሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት የስብከተ ወንጌል ኃላፊ በመሆን አገለግሎታቸውን በሰፊው ጀምረዋል። በዚያ አጭር የአገልግሎት ቆይታቸውም በተለይ በናዝሬት ከተማ በሚገኙ አድባራትና ገዳማት እየተዘዋወሩ በማስተማር በጠለቀ ትምህርታቸው ሕዝቡን እያረሰረሱና፣ ነፍሳቸውን በወንጌል እየማረኩ ሐዋርያነታቸውን አስመስክረዋል። ይሁን እንጂ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት ለከፍተኛ አገለግሎት ወደ ቅድስት ሀገር ኢሩሳሌም ተላኩ። በዚም

በ1982 ዓ.ም. ለዘጠኝ ወራት ያህል በቆዩበት ጊዜ በኢየሩሳሌም ባሉ የኢትዮጵያ ገዳማት አባቶች ጋር በአንድነት በመሆን ከሰጡት ስራ አገልግሎት እና ታዛዥነታቸው አንፃር የቅዱስ ፊልጶስ ገዳም ቄሰ ገበዝ በመሆንም አገልግለዋል። ብፁዕነታቸው ከኢየሩሳሌም እንተመለሱ በ1983 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው ተመደቡ።

የዚያን ጊዜው አባ ኃይለኢየሱስ የዛሬው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በስብከተ ወንጌል ምዕመናን ለማገልል ለነበራቸው ሰፊ ምኞት ሁኔታው የበለጠ የተመቻቸው በዚህ ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል። ብፁዕነታቸው በደብረ ብሥራ ቅዱስ ገብርኤል እየተባለ በሚጠራው በዚህ ደብር በቆዩባቸው አራት ዓመታት ሕዝቡን ጠዋትና ማታ ከማስተማር በተጨማሪ ብዙ ወጣቶችን በሰንበት ትምህርት ኮርስ አዘጋጅተው በማሰልጠን ሰፊ ሥራ ሠርተዋል። ከሰንበት ት/ቤት አባላትም የተሻሉትንና ላቅ ያሉትን ደግሞ ልዩ ስልጠና በመስጠት ለሳባኪ ወንጌልነትና ግብረ ዲቁናውን እንዲማሩ በማድረግም ለዲቁና አብቅተዋል። በዚያም ታላቅ የስብከተ ወንጌል አዳራሽና በሰበካው በመካነ መቃብርነት ያገለግል በነበረው ቦታ የመካኒሳ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን አሠርተዋል።

ከዚህ ስራ አገለግሎት በኋላ በ1986 ዓ.ም ወደ መርካቶ ደብረኃል ቅዱስ ራጉኤል ተዘዋውረው ለአጭር ጊዜ ካገለገሉ በኋላ ኅዳር 4.ቀን 1987 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የከምባታ፣ ሀድያ እና ጉራጌ አኀጉረ ስብከት ጳጳስ ሆነው ተሾሙ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእነዚህ በተሾሙባቸው አኀጉረ ስብከት ላይ ደርበው የተለያዩ ኃፊነቶችን እየተቀበሉ ቤተክርስቲያናቸውን ያለ ዕረፍት አገለግለዋል። ከዚህም ውስጥ በ1991 ዓ.ም. በአውሮፓ የነበረችውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቶያን ጊዜያዊ ችግር ፈትተው እና ሕዝቡን አስተምረው እንዲመለሱ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት እንግሊዝ ለንደንን ማረፊያ በማድረግ ስራ አገለገሎት ሰጥተዋል። ከእንግሊዝ ለንደን በተጨማሪ፣ በአየርላንድ፣ ጣሊያን፣ በሆላንድ፣ በቤልጂየም፣ በግሪክ፣ በስዊዘርላንድ ሰፊ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሰጥተዋል። በተለይም የስዊዘርላንድ ከተሞች በሆኑት በጄኔቭ፣ በዙሪክ፣ በሉዛን እና በበርን ሰፊ ሐዋርያዊ አገልግሎት አበርክተዋል። በዚህ አጭር ቆይታቸውም በሆላንድ  የቅዱስ ገብርኤልን እና በኦስትርያ ቪየና የቅድስት ኪዳነ ምሕረትን አብያተክርስቲያናትን ባርከው ለአገለግሎት አብቅተዋል። የስድስት ወር

የአውሮፓ አገለግሎታቸውን ተወጥተው ከተመለሱም በኋላ በሀገረ ስብከታቸው ላይ ደርበው የምዕራብ ሸዋን ሀገረ ስብከትን ለአንድ ዓመት አገልግሎት ሰጥተዋል።

ከዚህም በኋላ ከግንቦት 1996 ዓ.ም.እስከ ግንቦት 1999 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ በመሆን ቅድስት ቤተክርስቲያናቸው የጣለችባቸውን ኃላፊነትና አደራ በአግባቡ ተወጥተዋል። ከዚህም ጊዜ በኋላ አንጉረ ስብከታቸው ላይ በመሆን የተለመደ ሰፊ አገልግሎታቸውን ሲያበረክቱ ቆይተዋል። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ አገልግሎታቸውን በሚከተለው መልኩ ይሆናል።

በተጠቀሰው ሰፊ ሥራዎች ዋና ዋናዎቹን ብቻ መርጠን እናቀርባለን።

1. ከንባታና ሐድያ የሀገረ ስብከቱን ጽ/ቤት አስገንብተዋ። መንበረ ጵጵስናውን ማሳደስና ቅጥሩንም በማስቀጠር አስከብረዋል።
- በመንበረ ጵጵስናውም የኅልጎታ መድኃኒዓለምን ገዳም ቤተክርስቲያን አሠርተዋል። ለደብሩ ገቢ ማስገኛ የሚሆኑ ቤቶችንም አሰርተዋል። በተጨማሪም ሁለት ወፍጮዎችን አስገዝተው ሰጥተዋል። ለመትከያም መሬት በ50,000 ብር ገዝተው ቤቶቹንም አሠርተዋል።
- በብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ስም የተሰየመ የአንደኛ ደረጃ ዘመናዊ ት/ቤት እና ‹‹ስመከ ሕያው ዘእይመውት ጎርጎርዮስ ካልዕ›› በሚል የተሰየመ ሁለገብ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ አሠርተዋል።
- በሀገረ ስብከቱ ግቢ ውስጥም ‹‹ጎርጎርዮስ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ት/ቤት›› በሚል ት/ቤት ከፍተዋል።
- 900 ካ.ሜ. ከከተማው ማዘጋጃ ቤት በመቀበል ዘመናዊ ሕንፃ እና ት/ቤት እስከ ቅጽሩ ድረስ አሠርተዋል።
- በዚሁ ሀገረስብከት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን ከማሳነፃቸውም በላይ የገቢ ማስገኛ ሕንፃዎችን፣ የአብነት ት/ቤቶችን፣ ወጣቶችን በማሰልጠን ለሰባኪ ወንጌልነት እና ለክህነት አብቅተዋል።
- በትርቡ በሆሣዕና ቡሽና አካባቢ በዛፍ ላይ በተገለፀው ሥዕል መነሻነት ቦታውን ተረክበው በመገደም ሰፊ ሥራ ለመሥራት የተለያዩ ፕሮጀክቶች መተግበር ጀምረው ነበር።

## በጉራጌ ሀገረ ስብከት ከተሠሩት ሥራዎች በከፊል

- በወልቂጤ ከተማ እንብርት ላይ ይገኝ የነበረውን 1,360 ካ.ሜ ተረክበው የሀገረ ስብከቱን ጽ/ቤት አሠርተው በቦታው ላይ ዘመናዊ መንበረ ጵጵስና ለማሠራት ዲዛይኑ ተጠናቅቆ የመሠረተ ድንጋይ ተጥሏል።
- ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ በወልቂጤ ከተማ 4,500 ካ.ሜ ተረክበው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታው በመፋጠን ላይ ይገኛል።
- በወልቂጤ ደብረ ሲና ቅዱስ ገብርኤል አጠገብ የሚገኘውንም ሰፊ ቦታ ለሀገረ ስብከቱ የልማት ማስፋፊያ ይሆን ዘንድ ከመንግስት ተረክበዋል።

ታሪካዊውን የምሁር ኢየሱስን ገዳም ወደ ታሪካዊነቱ ታላቅነቱ ለመመለስ ከሠሩት እጅግ መጠነ ሰፊ ሥራም የሚከተሉትን ለአብነት ያህል ብቻ መጥቀስ ይቻላል።

1. ከቅዱስ ሲኖዶስ አስፈቅደው በገዳሙ አዳሪ ት/ቤት ከፍተዋል። በቂ የሆኑ የመማሪያ፣ የመመገቢያ እና የማደሪያ ቤቶችንም ገንብተዋል።
2. ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የአብነት ት/ቤቶችን በማቋቋም በቅኔ፣ በአቋቋም፣ በቅዳሴ እና በሐዲሳት ትርጓሜ እጅግ ብዙ ደቀመዛሙርት እንዲመረቁ አድርገዋል።
3. ለሰባት አብያተ ጉባኤያትም (ለንባብ ቤት፣ ለቅዳሴ ቤት፣ ለቅኔ ቤት፣ ለአቋቋም ቤት፣ ለድጓ ቤት፣ ለትርጓሜ እና ቤተ እንዚራ የሚባል የበገና ቤቶችንም) አሠርተዋል።
4. የገዳሙ ዋና ዋና ቅርሶች የሚጠበቁበት ዘመናዊ ሙዝየም አሠርተዋል።
5. በገዳሙ እንግዶች ማረፊያ የሚሆኑ ባለ 13 መኝታ ክፍል እና ጽርሐ ጎርጎርዮስ የተሰኘ አዳራሽ ያለው ሕንፃ አሠርተዋል።
6. የገዳሙ መናንያት የተግባር ዕድ ውጤቶች መሸጫ ቤትም አሠርተዋል።
7. ይህን ቦታ ከደብርነት ወደ ገዳምነት ያሸጋገሩት ኢትዮጵያዊ ፃድቅ አቡነ ዜና ማርቆስ በተገደሉበት ዋሻ አጠገብ በሚገኘውና ከራሱ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ የአቡነ ዜና ማርቆስን ቤተክርስቲያን አሠርተዋል።
8. የገዳሙንም አዳራሽ በከፍተኛ ወጭ በማሳደስ ለአገልግሎት አብቅተዋል።
9. የ36ቱን ቅዱሳት አንስት አሠረ ፍኖት በተከተሉት በገዳሙ መናንያት የመኖሪያ ሕንፃ አሳንፀዋል።

10. በገዳመ ያሉ አባቶች ከሚኖሩበት አጠገብ በገዳሙ ዘመናዊ ት/ቤት እንዲከፈት አድርገዋል። ይህ ት/ቤት በዚህ አመት የ8ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የሚያስፈትን ሲሆን ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለማሸጋገር በዝግጅት ላይ ይገኛል።
11. ችግረኛ እና ወላጆች የሌላቸው ልጆች እየተማሩ የሚያድጉበት ትምህርት ቤት ተከፍቶ በበጎ አድራጊዎች እየተረዱ የሚያድጉ 100 ሕፃናት በመማር ላይ ይገኛሉ።
12. በገዳሙ ለስብከተ ወንጌል ሥልጠና የሚመደቡ ሠልጣኞች የሚገለገሉባቸው ሁለት ሕንፃዎችን አሠርተዋል።
13. በገዳሙ ለሚኖሩ የአብነት መምህራን መኖሪያ የሚሆን ባለ 8 መኝታ ቤት እና የእንግዳ መቀበያ ክፍሎች ያሉት አንድ ብሎክ አሰርተዋል።
14. ለገዳሙ አስተዳደር በጽ/ቤትነት የሚገለግል G+1 ቤት አሠርተዋል።
15. ገዳሙ በተፈጥሮ ደን የተከበበ ቢሆንም ከባሕር ዛፍ አንስቶ እንደ ቡና፣ ማንጎ፣ አቡካዶ እንሰትና መሰል ፍራፍሬዎችና ዕፅዋት በብዛት አስተክለዋል።
16. የወረዳው ከተማ ከሆነችው ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ገዳሙ በር የሚደርሰውን መንገድና አንድ ከፍተኛ ድልድይ የአካባቢውን ሕዝብ በማስተባበርና ክክልሉ መንግሥት ጋር በማስተባበር በተሻለ ደረጃ አስጠግነዋል።
17. ገዳሙን ከልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለገዳሙና ለአካባቢው ንጹሕ የመጠጥ ውሃ እና ከክልሉ መንግሥት ጋር በመሆን ደግሞ የ24 ሰዓት የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆን አስደርገዋል።
18. በወረዳው ከተማ ሐዋርያት ከመንግሥት በተረከቡት ሰፊ ቦታም አፀደ ሕፃናት አስከፍተው የከተማውን ሕዝብም አገልግሎት እንዲያገኝ አስችለዋል።
19. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቱን አገለግሎት ለማስቀጠልም አንድ ብሎክ ሕንፃ አሠርተው በሚቀጥለው ዓመት አገልግሎት እንደሚጀምር ይጠበቃል።
20. የገዳሙን እንግዶች በተሻለ አገልግሎት ለመቀበል እንዲቻል በወረዳው ከተማ ቦታ ተረክበው የግንባታ መሠረቱ ተጥሏል።
21. በወልቂጤ ከተማ ለት/ቤት በተረከቡት 10,000 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ት/ቤቱን ሥራ አስጀምረው በአሁኑ ጊዜ 665 ተማሪዎችን በመቀበል ሕዝቡን በማገልገል ላይ ሲገኝ በአሁኑ ጊዜ በቦታው G+4 ሕንጻ በመሠራት ላይ ይገኛል።

22. ከዚህም በተጨማሪ ከሰበታ መዘጋጃ ቤት 10,000 ካ.ሜ. ቦታ ተቀብለው ት/ቤት አስገንብተው በአሁኑ ጊዜ ከኒርሰሪ እስከ 3ኛ ክፍል ድረስ በማስተማር ላይ ይገኛል።
23. ለዚሁ ገዳም የገቢ ማስገኛ ይሆን ዘንድ በአዲስ አበባ ለቡ በሚባል አካባቢ በ640,000 ብር ቦታ በመግዛት G+4 ሕንፃ በመገንባት ላይ ይገኛሉ።

## ለምድረ ከብድ አቡነ ገ/መንፈስ ገዳም

1. ገዳሙን በመናንያኑ እንዲተዳደር ከማድረግም ጀምሮ አስተዳደራዊ ለውጦችን በማምጣት አጥጋቢ ፍሬ አስመዝግበዋል።
2. በገዳሙ ለሚመጡ እንግዶች ማረፊያ የሚሆን ባለ 13 ክፍል ማረፊያ ቤት ከእነ አዳራሹና ሌሎች ክፍሎች ጋር አሠርተዋል።
3. ወደ ገዳሙ የሚያስገባውን 18 ኪ.ሜ. መንገድ አይሪሽ ከተባለ የውጭ ድርጅት በመረዳት አስጠግነዋል።
4. የገዳሙን መናንያት በሰበታ ጌቴ ሰማኔ ቤተ ደናግል እንዲሰለጥኑ አስደርገው በተግባረ ዕድ እንዲሰማሩ አድርገዋል።
5. የገዳሙ መናኞችን ቤት እንዲሠራ አስደርገዋል።
6. የገዳሙ ቤተክርስቲያን ከሀገሪቱ ቅርሶች አንዱ በመሆኑ ያለ ቱሪዝም ፈቃድ ሊታደስ የማይችል በመሆኑ ለብዙ ዘመናት በመቆየት ለዕርጅና ተዳርጎ ነበር። እርሳቸው ከመንግስትን በማስፈቀድ የመንፈስ ልጆቻቸውን በማስተባበር አሳድሰውታል፤ በገዳሙ ያለችውን የእመቤታችንንም ቤተክርስቲያን በአዲስ መልክ አሠርተዋል።
7. ለገዳሙ የ24 ሰዓት የመብራት አገልግሎት እንዲያገኝም ከመንግስት ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ፈቃዳቸው ተፈፅመውላቸዋል።
8. በገዳሙ ለሚገኙ የአብነት መምህራንና ተማሪዎች መገለገያ የሚሆን የመማሪያ፣ መመገቢያ እና ማደሪያ ምግብ ማብሰያና መፀዳጃ የያዘ ህንፃ አሠርተው መጋቢት 5 ቀን 2002 ዓ.ም. ተመርቋል።
9. የገዳሙን የንጹሕ የመጠጥ ውሃ ችግር ለመፍታት ባደረጉት ከፍተኛ ጥረትም በመጀመሪያ ከልማት ኮሚሽን ድጋፍ ለመጠየቅ የዝናብ ውሃ ማጣሪያ ታንከር ከአስመጡ በኋላ ከበጎ አድራጊ ልጆቻቸው አማካኝነትም በ20,000 ብር የተገዛ ፋይበር ታንከር እንዲገጠም አድርገዋል።

10. በጎጃሙ 4 መምህራንና ከ20 ደቀመዛሙርት ከጠቅላይ ቤተክህነት፣ ከማህበረ ቅዱሳንና ከጎጃሙ በጀት በመጠቀም ቤተክርስቲያን ተተኪ አገልጋዮች እንዲታጣ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በአዲስ አበባ የሚኖሩ የሀገረ ስብከቱን ተወላጆች በማስተባበርም

ሀ. በሶዶ ክስታኔ ወረዳ

5 አብያተ ክርስቲያናት እና አንድ አዳሪ መንፈሳዊ ት/ቤት

ለ. በመስቃንና ማረቅ ወረዳ

4 አብያተ ክርስቲያናት

ሐ. በምሁርና አክሊል

4 አብያተ ክርስቲያናት

መ. በእዣ ወረዳ

5 አብያተ ክርስቲያናት

ሠ. በቸሃ

5 አብያተ ክርስቲያናት

ረ. በእንደጋኝ ወረዳ

4 አብያተ ክርስቲያናት

ሰ. በእነሞርና ኢነር

4 አብያተ ክርስቲያናት

ሸ. በጌታ ወረዳ

3 አብያተ ክርስቲያናት

ቀ. በጉመር

3 አብያተ ክርስቲያናት

ተ. አበሽጌና ቀቤና ወረዳ

1 አብያተ ክርስቲያናት

ቸ. በመንበረ ጵጵስናው

2 አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል።

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ወቅትም

1. የጠቅላይ ቤተክህነቱን ጽ/ቤት ባለ 4 ፎቅ

2. ስልሣ ሊቃነ ጳጳሳት ማረፊያ የሚሆን ባለ 4 ፎቅ

3. ለቅዱሳን ፓትርያርኮች ማረፊያ የሚሆን ባለ 2 ፎቅ ገስት ሐውስ
4. አሁን ለቤተ ክርቲያኒቱ ዋና ሙዝምም የሆነው ሕንጻ ዕድሳት እና
5. በጠቅላይ ቤ/ክህነት ሠራተኞችና ለአባቶ ማረፊያ የሚሆን ካፍቴርያ አሳንፀዋል።

ብፁዕነታቸው በዚህ አጭር ታሪካቸው ያልተጠቀሱ ሰፊ ሥራ በመሥራት ለቤተክርስቲያናቸው ሰፊ አገልግሎት ሲፋጠኑ ከኖሩ በኋላ ባደረባቸው ሕመም ይድኑ ዘንድ በፀበል እና በሕክምና ሲረዱ ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ50 ዓታቸው ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. ከሌሊቱ በዘጠን ሰዓት በሰላም አርፈዋል።

በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅዱስ ፓትርያረኩ፣ ብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና የመንፈስ ልጆቻቸው ባሉበት ጸሎት ፍትሐት ሲደረግላቸው ካረፈደ በኋላ ከስድስት ሰዓት በኋላ ጉዞ ወደ ወልቂጤ ተደረገ። በሀገረ ስብከታቸው መንበረ ጵጵስና በደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ትንሽ ዕረፍት ተደርጎ በቅዱስ ፓትርያርኩ መሪነት ጸሎተ ፍትሃት ተደርሶ ማታውኑ ጉዞ ወደ ምሁር ገዳመ ኢየሱስ ተደርጓል ከአዲስ አበባ ጀምሮ በእንባ ሲራጭ የዋለው ሕዝበ ክርስቲን በወልቂጤ፣ በሐዋርያት ከተማ እና በገዳሙ እጅግ በመሪር ሐዘንና እንባ እየተቀባበለ ማታ ከምሽቱ 1 ሰዓት ተወልደው ባደጉበት ከዲቁና እስከ ስና ባገለገሉበት በታላቁና ጥንታዊው ገዳም ምሁር ኢየሱስ ገብተ ካደረ በኋላ ሌሊቱን በሰዓታትና በማኅሌት ጸሎተ ፍትሐቱ ሲደርስ አድሯል።

ዛሬ ሰኔ 15 ቀን ጸሎተ ፍትሐቱ ሲደርስ ውሎ ጸሎተ ቅዳሴ ከተደረገ በኋላ ብፁዐን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ እጅግ በርካታ የሆነ ከሀገረ ስብከቱ የተለያዩ ከተሞች ከአዲስ አበባ፣ ከተለያዩ አቅራቢያ ከተሞች የተሰባሰቡ ምእመናን በተገኙበት በደከሙበት ገዳማቸው ከቀኑ 8:00 ሰዓት በክብር ዐጽማቸው እንዲያርፍ ተደርጓል።

ለእግዚአብሄር ክብር ይሁን !!!!!